ቀን፡ 02/08/2014

# ለዲያስፖራ ኗሪ  ኢትዮጵያውያን በሙሉ።

## የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ)ለስድብና ለማዋረድ ሥራ በክፍያ ያሰማራቸው ቅጥረኛ ባንዳዎችን እንዋጋ!!

ለሃገርና ለሕዝብ የቆሙ ግለሰብ ኢትዮጵያውያንን፤ ድርጅትና፤ ተቋማትን እያሳደዱ እንዲሰድቡና እንዲያዋርዱ ወያኔ አሰልጥኖ ያሰማራቸው ቅጥረኞች ሕዝብን ስይፈሩና ሳያፍሩ የባንዳነት ተግባራቸውን ቀጥለውበት ይገኛሉ።

የኢትዮጵያ መንግሥት የሚል ስያሜን የያዘው የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ) እነዚህን ተሳዳቢ ቅጥረኞች ያሰማራው የቻይና መንግሥት የኮሚንስት ፓርቲውን አመራር የሚቃወሙና የሚተቹ ግለሰብና ተቋማትን ለማሸማቀቅ ሲል አቋቁሞት የነበረውን የ50 ሳንቲም ፓርቲ (50 Pence Party ) ዘዴን በመውረስ ሲሆን ዓላማውም ለወያኔ የማይመችን ኢትዮጵያዊ ግለሰብ፤ ማህበረሰብንና ተቋምን ሁሉ በመስደብ በማዋረድና በሃሰት ክስ በማሸማቀቅ ቅስሙን ሰብሮ ተገዢ ለማድረግ ነው።

የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ) ይህንን ከቻይና አገዛዝ የወረሰውን የአዋርደህ ግዛ ዘዴ ሥራ ላይ ለማዋል ያፈለገበትም፤ በሃገር ውስጥ የአገዛዝ ሥርዓቱን የሚቃወሙ፤ ለሥርዓቱ የማይገዙና የማያጎበድዱ ሃገርና ሕዝብ ወዳድ ግለሰቦችና ቡድኖችን  ሁሉ በፌደራል ፖሊስና በደህንነት ኃይል እያነቀ መግረፍ፤ ማሰቃየት፤ ማሰርና ከዛም ካለፈ በመግደል ፀጥ የማድረግ እርምጃው በተጨማሪ ይህንን ለማድረግ በማይችልበት ወቅትና አካባቢ በተለይም ደግሞ በውጪ ሃገር በሚኖረው ኢትዮጵያዊ ላይ ተፈጻሚነት እንዲኖረው በማሰብ ለመሆኑ በየጊዜው የአገዛዝ ሥርዓቱን እየከዱ የሚኮበልሉ ባለሥልጣናት ጭምር ያረጋገጡት ጉዳይ ነው።

በዚህ የአዋርደህና አሸማቀህ ግዛ ዘዴ መሠረትም የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ) በተለይ በዲያስፖራው ኢትዮጵያዊ ላይ ያነጣጠሩ ዌብ ሳይቶችን፤ ብሎግ እና አያሌ የሶሻል ሚዲያ መድረኮችን በመክፈት አገዛዙ በጠላትነት የፈረጃቸው ግለሰቦች፤ ቡድን እና ተቋማት ላይ የተለያዩ ስብዕናን የሚያረክሱ ስድቦችን፤ የሃሰት ውንጀላዎችንና ክሶችን በማዥጎድጎድ ግለሰብና ተቋማቱ ቅስማቸው ተሰብሮ ፈርተውና ተሸማቀው እንዲኖሩ ለማድረግ  የስድብ ቅጥረኞቹን አሰልጥኖ በሕብረተ ሰቡ ውስጥ በማሰማራት ከፍተኛ ገንዘብ እየከፈላቸው በሙሉ ሰዓት ሰራተኝነት ይህንኑ የስድብና የማዋረድ ተግባራቸውን በማከናወን ላይ ይገኛሉ።

እነዚህም በዲያስፖራው ኢትዮጵያዊ ውስጥ በመሰግሰግ በኮሚኒቲም ይሁን፤ በፓሊቲካና በሲቪክ ድርጅቶች፤ እንዲሁም በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ ሳይቀር ለሃገርና ለሕዝብ የቆሙ ሃቀኛ ኢትዮጵያውያንን ስም በማብጠልጠል የሚሰድቡና የሚያዋርዱ የወያኔ ቅጥረኛ ባንዳዎች በስራቸው እየተጋለጡ ይገኛሉ።

በዚህ መሠረት በአሁኑ ወቅት ሥራቸውም ሆነ ማንነታቸው በግልጽ ከታወቁት የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ) የሙሉ ሰዓት ቅጥረኛ ተሳዳቢ ሰራተኞች ውስጥ በ1ኛ ደረጃ የሚጠቀሰው ኗሪነቱ በእንግሊዝ ሃገር በለንደን ከተማ የሆነው አቶ እንዳለ ወንዳፍራሽ ወይም ራሱን (Endex) እያለ የሚጠራ ግለሰብ ነው። እንዳለ ወንዳፍራሽ ከታች በፎቶው ላይ እንደሚታየው የቅጥረኛ ባንዳነት ሥራውን ለመሸፈን ሲል ሁሌም ኮፊያ፤ ከራሱ ላይ ጥቁር መነጽር ደግሞ ከዓይኑ ላይ አይለይም።



ይህ ግለሰብ ከተባባሪዎቹ ጋር በመሆን Speakers corner በሚል መጠሪያ የቫይበር መልዕክት መለዋወጫ (viber chat group) በማቋቋም፤ በዛ አማካኝነት ከትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ) የሚተላለፍለትን የቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ሥራ እያቀነባበረ በማሰራጨት ሌት ተቀን በመሥራት ላይ የሚገኝ ነው።

ከዚህም በተጨማሪ ይኸው ግለሰብ የተለያዩ ተንቀሳቃሽ ምስሎችን እያቀነባበረ በተለይም ደግሞ "ሰዓት ካልሆነ በስተቀር አንዳችም እውነት አይናገርም" ተብሎ ሕዝብ አንቅሮ የተፋውን የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን፤ Ayga Forum, Tigray On Line የተባሉ የትግራይ ነጻ አውጪ ድርጅት ደረቅ ፕሮፓጋንዳ ማሰራጫ ድህረ ገጾችን በመጠቀም ቪዲዮዎችን በYouTube በመልቀቅ ግለሰቦችን፤ ቡድኖችን፤ የፓለቲካ ድርጅቶችንና ተቋማትን ይሰድባል ያዋርዳል በሃሰት ይወነጅላል።

ይህ ግለሰብ ሌላው ቀርቶ በቅርቡ በሳውዲ አረቢያና በሌሎች አረብ ሃገራት ኢትዮጵያውያን ሲገደሉ፤ ሲደፈሩ፤ ሲዘረፉና እንደ ሰው ሳይሆን የውሻን ክብር እንኳ የሚሰጣቸው ጠፍቶ፤ ዜጋዬ ብሎ የሚቆምላቸው መንግሥት አጥተው ከፍተኛ ሰቆቃ ሲፈጸምባቸው የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር የአገዛዝ ሥርዓት ሥራ እንዳይጋለጥና እንዳይወቀስ ሽፋን ለመስጠት ሲል <u>በኢትዮጵያውያኑ ላይ የሚደርሰው በደልና ሰቆቃ ሁሉ ራሳቸው ኢትዮጵያኑ የሰሩት ሕገ ወጥ ሥራ ውጤት እንጂ የኢትዮጵያውን አገዛዝም ሆነ የሳውዲን መንግሥት የሚያስጠይቅና የሚያስወቅስ ነገር የለበትም በማለት ታሪክ ይቅር የማይለው ከፍተኛ የሃሰት ፕሮፓጋንዳ ሲያሰራጭ ነበር።</u>

ኢትዮጵያን ጨምሮ በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በሳዑዲ አረቢያ የሚገኙ ወገኖቻቸው ላይ የሚደርሰው በደልና ግፍ አስቆጭቷቸውና አሳዝኗቸው በዓለም ዙሪያ ያሉ የሳዑዲና የኢትዮጵያ ኤንባሲዎችን በማጨናቀቅ ቁጣቸውን በመግለጽ ለዓለም መንግሥታትና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች ሁሉ አቤት ሲሉ እንዳለ ወንዳፍራሽና መሰል የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር ቅጥረኛ ተሳዳቢዎች ግን የኢትዮጵያዊውን ተቃውሞ ለማኮሸፍና ዋጋ ለማሳጣት ልዩ ልዩ አፍራሽ የፕሮፓጋንዳ ጽሑፎችን በሶሻል ሚዲያዎች ላይ ያስተላልፉ ነበር።

በወቅቱ እንዳለ ወንዳፍራሽ <u>ምድርን ያጨቀየው የኢትዮጵያን ደም ሳያሳሳው፤ ያለማንም ጠያቂ በየሜዳው እንደውሻ እየተገደሉ የተጣሉትና በመጣል ላይ ላሉት ኢትዮጵያን ሕይወት ምንም ግድ ሳይሰጠው፤በየከተማና ገጠሩ በሳዑዲ ወጣቶች ታፍነው በህብረት የሚደፈሩት (Group rape) የሚደርስባቸው ሴት ኢትዮጵያውያን ሰቆቃ ሳይሰማው፤</u>

ከትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ) የተሰጠውን ግዳጅ በመከወን የሚሰጠውን ምጽዋት ለመቃረም ሲል የሳዑዲ መንግሥትና ለሳዑዲ ወጣቶች ተቆርቋሪ በመሆን ያሰራጭ ከነበረው Viber text መልዕክት ውስጥ ቀጥሎ የተመለከተው ይገኝበታል።


ይህና የመሳሰለው የViber text መልዕክት ለመሠረዝና ለመደለዝ አዳጋች በመሆኑም የዚህን ቅጥረኛ ባንዳና ተባባሪዎቹ የወቅቱ ተግባራቸው ለታሪክ ተይዞ የሚኖር ይሆናል።

## Viber text

Sender: Endex (Endale Wondafrash

**Date: Thursday 21 November 2013**

**Time: 10.57 am**




<u>(Copy and pest የተደረገው የእንዳለ ወንዳፍራሽ የViber text መልዕክትን ደግሞ ከዚህ በታች ይመልከቱ።)</u>

Saudi youth have denounced the fabricated video clip titled 'Hell on Earth' being circulated on social media by Ethiopian activists to tarnish the image of Saudi Arabia following its crackdown on illegals.

Illegal Ethiopians sought to portray a negative image of Saudi Arabia's handling of the rioting perpetrated by them in Riyadh and Jeddah.

The Saudis posted photos of actual events that had taken place in recent days, reiterating how well Saudi forces handled the mob of illegals.

"What has been circulated by the Ethiopian activists online is false and was aimed at tarnishing the Saudi image," one Saudi said.

Most of the events depicted in the Ethiopian video had taken place in countries like Lebanon and Yemen a few years ago, he said. "This shows that the video clip was concocted and has nothing to do with the truth."

ይንን የመሰለ ባንዳነት ከቶ በኢትዮጵያዊውያን ታሪክ ውስጥ ታይቶና ተሰምቶ ያውቅ ይሆን?

እንዳለ ወንዳፍራሽና ግብረ አበሮቹ ይህንን የሚያደርጉት ከታች የሚታየውን የመሰለ በርካታ የኢትዮጵያውያንን ሰቆቃ የሚያሳይ ምስል እያዩ ሳይራሩ የአረመኔነት ባህሪን በመላበስ ነበር።



















(ይህ ከላይ የሚታየው ለምልክት ያህል ሲሆን በሳዑዲ አረቢያ ወገኖቻችን የደረሰባቸውን ሰቆቃ ምስልና የበለጠ መረጃ ለማግኘት ከታች ያለውን ሊንክ ይጠቀሙ።)

https://www.google.co.uk/search?q=ethiopian+in+saudi&tbm=isch&tbo=u&source=univ&sa=X&ei=3WzaU9rpEaS80QXT34CwAg&ved=0CB8QsAQ&biw=1378&bih=629

ከላይ የተገለጸው ቅጥረኛው ባንዳ እንዳለ ወንዳፍራሽና የተባባሪዎቹ ተግባር ከበርካታ ወራት በፊት የተፈጸመ ታሪክ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ደግሞ እነዚህ ባንዳዎች የሚከተለውን ድርጊት በማከናወን ላይ ይገኛሉ።

አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በሕገ ወጥ መንገድ ከየመን ታፍኖ ተወስዶ በትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ) የሰቆቃ እሥር ቤት መግባቱና ለስቃይና መከራ መዳረጉን በመስማት ያላዘነና ያልተቆጭ ኢትዮጵያዊ ባይኖርም እንዳለ ወንዳፍራሽና ግብረ አበሮቹ ግን በአቶ አንዳርጋቸው መያዝ በደስታ በመፈንደቅ ጮቤ እየረገጡ ሌላ አረመኔያዊ የባንዳነት ድርጊት በማከናወን ላይ ይገኛሉ።

እነዚህ ቅጥረኛ ባንዳዎች ተልኳቸውን በማሳካት የሚጣልላቸውን ፍርፋሪ ለመቃረም ሲሉ የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባርን (ወያኔ) ልሳን ከሆነው ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት በመፍጠር አገዛዙ ለሃገርና ለሕዝብ የሚታገሉ የፓለቲካ ድርጅቶችን፤ ተቋማትንና ግለሰቦችን ለማሸማቀቅ ብሎ በቴሎቪዥን ያስተላለፈውን የሃሰት ፕሮፓጋንዳ እያቀነባበሩ በቪድዮ በመልቀቅና የViber text ኢትዮጵያዊውን ለማሸበር በመጣር ላይ ይገኛሉ።

የለንደን ነዋሪ ኢትዮጵያውያን እንደሚያቁት ሁሉ ከአሁን በፊትም ይኸው እንዳለ ወንዳፍራችና ግብረ አበሩ የሆነው ግርማ ወልደ ማርያም ከትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ) የደህንነትና የኤምባሲ ተወካዮች ጋር በመተባበር Ethio London TV የሚል በሳምንት አንድ ቀን ለአንድ ሰዓት የሚተላለፍ የቴሌቪዥን ስርጭት በማቋቋም የETV ቅርንጫፍ ሆነው ዲያፖራውን በፕሮፓጋንዳ ለማደንቆር ሙከራ ያደረጉ ሲሆን ነገር ግን የቴሌቪዥን ስርጭቱ አዳማጭና ተመልካች በማጣቱ ምክንያት ፈጥኖ ሊቋረጥ ችሏል።


ይህ የወያኔ ተለጣፊ የቴሊቪዥን ጣቢያ ምሥረታ በከሸፈ ማግሥት ግን በዲያስፖራው ኢትዮጵያዊ ጥረትና ድካም ዛሬ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ልሳን እና አለኝታ የሆነው ኢሳት (ESAT) ተቋቋመ። የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ) ይህንን የሕዝብ ልሳንና አለኝታ የሆነ የሚድያ ተቋም በእንጭጩ ለማኮላሸትና ለማውደም አያሌ ጥረት አድርጎ ኢሳትን መገደብ ያልቻለ ቢሆንም አሁንም ድረስ ግን ጥረቱን አላቋረጠም።

***<u>የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ) ቅጥረኛ ባንዳ ግርማ ወልደ ማርያም ምስል።</u>***



***<u>ግርማ ወልደማርያም በUK ኗሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን በገንዘባቸውና በድካማቸው ጥረውና ግረው የገዙትን የለንደኗን ደብረ ጽዮን ማርያም ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ለወያኔ አገዛዝ አሳልፎ በመስጠት ጽጽሰና እና ጥቅማ ጥቅምን ለማግኘት ሲል ሕዝቡን ከከዳው የለንደኑ ዲያብሎስ አባ ግርማ ከበደ ጋር በመሆን የግንቦት 20ን የወያኔ በዓል ለንደን በሚገኘው ኤምባሲ ውስጥ ከቀርበታው የወያኔ አምባሳደር ብርሃኑ ኋላ ተሰልፈው ሻፓኝ ሲጠጡ የሚያሳየው ምስል ደግሞ እንደሚከተለው ይታያል።</u>***

***<u>ሁሉም የወያኔ ቅጥረኛ ባንዳዎች በየደረሱበት መከራከሪያ ነጥባቸው "እኔ ወያኔ አይደለሁም" የሚል ነው። ኢትዮጵያዊ ሆይ ንቃ!! ወያኔ አይደለሁም ብቻ ሳይሆን ወያኔን በመስደብና በማጣጣል የሕዝብና የሃገር ታማኝ መስለው ሕዝብ ውስጥ ሰርገው እንዲገቡ ወያኔ ሙሉ ፍቃድ ሰጥቷቸውልና በቃላት፤ ወይም በድሮ ድርጊታቸው አትሞኙ አሁን በሚሰሩት እንጂ።</u>***




***በምስሉ ውስጥ የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ) በበላይነት የሚቆጣጠረው የለንደኑ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ቄስ ከፍ ያለውና የሃገረ ስብከቱ ስራ አስኪያጅ ተብሎ በአገዛዙ የተሾመው ተወልደ ይገኙበታል።***

ቪዲዮውን ለመመልከት ሊንኩን ይጫኑ። https://www.youtube.com/watch?v=jgxmhytBjlw

እነዚህ ቅጥረኛ ባንዳዎች ከትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ) በሚሰጣቸው መመሪያና ትዕዛዝ መሠረት ዋንኛ ዒላማቸው አድርገው የያዟቸው አገዛዙ ጠላት ብሎ በአንደኛ ደረጃ በመፈረጅ እንደጦር የሚፈራቸው፤ ነገር ግን ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ አለኝታና ተስፋው አድርጎ የሚደግፋቸውን ተቋማት ነው።

**የጥቃት ዒላማ የተደረጉትም፡**

1ኛ) በትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር አፋኝ ሥርዓት አንዳችም የነጻ ሚድያ አገልግሎት እንዳያገኝ ታፍኖ ለሚገኘው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አይንና ጆሮ፤ ተስፋና አለኝታ ሆኖ የሚገኘው **የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥንና ራዲዮ ስርጭት ተቋም** (ESAT)፤ ሲሆን

2ኛ) **ግንቦት ሰባት ለፍትሕ ለነጻነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ ነው፡፡**

በተለይ ከላይ የተጠቀሱትን ሁለት ተቋማት የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ) ሽብርተኛ ብሎ በመፈረጅ ከፍተኛ ዘመቻ እንደ ከፈተባቸው ሁሉ ዛሬ እንዳለ ወንዳፍራሽና ግብረ አበሮቹም ስደተኛ ነኝ ብለው ነጻነትና የሕግ የበላይነት በሰፈነበት ሃገር ከስደተኛው ጋር እየኖሩ የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌን በጠላት እጅ መውደቅ ምክንያት አድርገው የቅጥረኝነት ዘመቻቸው ዋንኛ ዒላማ ያደረጉት በነዚሁ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ አለኝታና ተስፋ፤ ለትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር ግን መቅሰፍት በሆኑ ተቋማት ላይ ነው።

**እስቲ የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ) ሥልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቅባቸው ተግባራቱን እንይ፡**

1. ያልታጠቁና ምንም ዓይነት መከላከያ የሌላቸውን የ7 ዓመት ህጻን፤ የ70 ዓመት አሮጊት ወንድ ሴት ህጻን አዛውንት ሳይለይ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ንጹሓን ኢትዮጵያኖችን መጨፍጨፍ፤
2. አገዛዜን ተቃውመሃል፤ ወይም ትቃወማለህ በሚል የጠላውን በሺህ የሚቆጠር ኢትዮጵያዊ አስሮ በመግረፍ፤ በወንድ ብልት ላይ ድንጋይና የውሃ መያዣ በማሰር፤ በሴት ብልት እንጨትና ብረት በማስገባት በማሰቃየት አረመኔነቱ፤
3. ሴትን በኤች አቪ ታማሚ በማስደፈር፤ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ደግሞ ወንድን በወንድ ሳይቀር በማስደፈር፤
4. ጋዜጠኛ ብሎገር፤ ተማሪና አስተማሪ፤ ሰራተኛና ፓለቲከኛ ሁሉ አገዛዙን እስካልደገፈ ድረስ አሸባሪ በማለት፤ ራሱ ከሳሽና ፈራጅ በመሆን ወሂኒ ቤት በመጣል፤
5. አማራ ኦሮሞ፤ በማለት ዘር ለይቶ በማጥቃት ዘርን በማጥፋት፤
6. ስልጣን ላይ ለመኖርና የጎሳ የበላይነቱን ጠብቆ ለማኖር ሲል የሃገርን መሬትና ዳር ድንበር በመሸጥ፤ በመለወጥና አሳልፎ በመስጠት ነው።

ከላይ ከብዙ በጥቂቱ የተዘረዘርውና የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ) በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ የሚፈጸመው በደልና ሰቆቃ በስሚ፤ ስሚ የሚነገር ሳይሆን Amnesty International, Human right watch እና U.S DEPARTMENT OF STATE ሳይቀር በማስረጃ የተረጋገጠ ሃቅ ነው።

ከእነዚህ የአገዛዙን አረመኔያዊ ተግባር ከሚያጋልጥ መካከል ለአበነት ያህል በU.S DEPARTMENT OF STATE የወጣውን Human right watch: Ethiopia የሚለውን ከታች ያለውን ሊንክ በመጫን ያንብቡ።

http://www.state.gov/j/drl/rls/hrrpt/2010/af/154346.htm

**<u>ከሪፓርቱ መካከል ለቅምሻም ያህል ይህ ይገኝበታል።</u>** ***"horrific experiences at Maekelawi. They included lengthy nights of physical mistreatment, including: being made to lie on the ground, handcuffed, blindfolded, and in some cases naked, while interrogators wearing military boots stood on their chests; being whipped with wire and beaten on the head and the insides of their feet; being gagged, hung upside down, and beaten with electrical cords; being threatened with injection of HIV-infected blood; and being subjected to ethnic slurs"***

በአሁኑ ወቅት እንዳለ ወንዳፍራሽና ግርማ ወልደማርያና ሌላ ደግሞ ዲያቆን ነኝ የሚል መንገሻ መልኬ የተባለ ግለሰብ በለንደን ከተማ የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ) ቅጥረኛ ባንዳዎች በመሆን በሃገር ውስጥ የኢትዮጵያውያንን ሰብዓዊ መብትን ረግጦ ግፍና ሰቆቃ የሚያደርሰውን ሥርዓት በማጋለጥ ድምጹ ለታፈነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጽ የሆነውን የዲያስፖራ ኢትዮጵያዊ ትግል በእነሱ ስድብና ማዋራረድ ተሸማቆ ድምጹን አጥፍቶ እንዲኖር ለማድረግ በመጣር ላይ ይገኛሉ።

ኢሳትን፤ ግንቦት 7 እና በአጠቃላይ የወያኔ ደጋፊ ያልሆነውን ኢትዮጵያዊ ሁሉ በYou Tube ቪዲዮ ላይ እየወጣ የሚሳደብና ነገ እያንዳንዳችሁ እንደ አንዳርጋቸው አንገታቸው ታንቆ ትወሰዳላችሁ እያለ የሚፎክር ዲያቆን ነኝ ባዩ መንገሻ መልኬ።



በእርግጥም እነዚህን ቅጥረኛ ባንዳዎች ሕብረተሰቡ ዝም ብሎ ካለፋቸው ቀጥለው የወያኔን ፌደራል ፓሊስና ደህንነት በውጪ ሃገራት አቋቁመው የአዲስ አበባውን ማዕከላዊ ምርመራ እስር ቤት አምጥተው ለወያኔ አልገብር ያለው ኢትዮጵያዊ ላይ ሰቆቃ እንፈጽም ከማለት የሚመለሱ አይደሉም።

ኢትዮጵያኖች በስደት ሃገር ሃይማኖታቸውን፤ ባህላቸውንና ማንነታቸውን ጠብቀው ለትውልድ ለማስተላለፍ ሲሉ የሃይማኖት ተቋማትንና የኮሚኒቲ ማዕከሎችን መሥርተው ማደግ ሲጀምሩ የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር የራሱ ጎሳ በበላይነት የሚመራው ካልሆነ በስተቀር ሌላውን ስለማይቀበል በጎን ሌላ ተቀጥላ በማቋቋም ያንን የማይቀበልና ለአንድ

ኃሳ የበላይነት አልበረከከም ያለውን ኢትዮጵያዊ እንደነ እንዳለ ወንዳፍራሽ ያሉ ቅጥረኛ ባንዳዎችን መልምሎ በማሰማራት በኢትዮጵያዊነት ባህልም ሆነ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ በብልግና የተሞላ የስድብ ናዳ እንዲያወርዱበት ያደርጋል።

ይህም የሚደረገው በግብረ ገብነት ታንጾ በጨዋነት ያደገውን ኢትዮጵያዊ በማሳቀቅ ለእውነት ከመቆምና ስለ እውነት ከመስራት ሊያርቀው ይችላል በሚል የተሳሳተ ግምትና እምነት ነው።

ስለዚህ የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር (ወያኔ) እነዚህን ቅጥረኛ ተሳዳቢ ባንዳዎች በማሰማራትም ሆነ በሌላ መንገድ ነጻነትና ዲሞክራሲ በሰፈነበት በውጪ ሃገር የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ በማስፈራራት ማሸማቀቅ ሳይሆን ባንዳዎቹ ራሳቸው በሚሰሩት ሕገ ወጥና አሳፋሪ ተግባራቸው እንዲሸማቀቁና ለባንዳነት ድርጊታቸውም ተገቢውን ቅጣት እንዲቀበሉ በማድረግ ስደተኛው ኢትዮጵያዊ መብትና ነጻነቱን አስከብሮ በአንባ ገነናዊ አገዛዝ የሰብዓዊ መብቱ እየተገፈፈ በሰቆቃ ውስጥ ለሚኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነት በጥንካሬ በመቆም መታገል ይኖርበታል።

ኢትዮጵያ ለዘለዓላም ትኑር!!

አሰፋ ምን ተስኖት